# <u>የትኛው ነው አንገብጋቢው ጥያቄ?</u>

# <u>ኢሕ አፓ ታሪኩን መጻፍ ወይስ ባንገብጋቢው ጥያቄ ላይ መረባረብ?</u>

የሚድዌስቱ ሲራክ

**የኢትዮጵያ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ምንድነው?** ይህ ጥያቄ ትናንት ሲጠየቅ የነበረ ግን ትናንት መልስ ያላገኘ በመሆኑ ዛሬም የሚጠየቅ ጥያቄ ሆኗል፡፡ ይህ ጥያቄ ዛሬ መልስ ካላገኘ ለነገ መተላለፉ የማይቀር ይመስላል፡፡ የሚያስፈራው ግን ጥያቄው ከመመለሱ በፊት ኢትዮጵያ ታሪክ እንዳትሆን ነው!!! የድሮውን የኢትዮጵያን የቆዳ ስፋት ለታሪክ እንተወውና በቅርቡ ጂቡቲ እኮ የኢትዮጵያ አካል ነበረች፡፡ ኤርትራም የኢትዮጵያ አካል ነበረች፡፡ ዛሬ በምእራብ ኢትዮጵያ ያለው ድንበራችን ያለይገባኛል ጥያቄ የኢትዮጵያ መንግስት ነኝ በሚባለው ባዕድ አካል ለሱዳን እየተሸርሸረ ነው፡፡

ሳይቆይ ደግሞ የምስራቁም ድንበራችን ለሱማሌ እንደማይሰጥ ማረጋገጫ የለንም፡፡ በደቡቡም ኬንያ ተመሳሳይ እድል ይጠብቃታል፡፡ የኤርትራ በሕገወጥ መንገድ መገንጠል ሳያንስ የቀራት መሬት አለና ውሰጅ እየተባለች በመለመን ላይ ናት፡፡ የኦጋዴን ነጻ አውጭ ከተሳካለት የቻለውን መሬት ተሸክሞ ሊሰናበተን መንገዱን በማደላደል ላይ ነው፡፡

የኦሮሞ ነጻ አውጭም ለዘመናት ያልተሳካለትን ሕልም ለማስፈጸም የማይገለብጠው ድንጋይ የለውም፡፡ የትግራይ መንግስት ለመመስረትም ወያኔ ምኞቱ አልደረቀም፡፡ የማይናቅ የቆዳ ስፋት ያለው የመሃል መሬታችን ቢያንስ ለ99 አመታት ሕንድ፣ ቻይና፣ሳውዲ አረቢያ . . . ቅኝ ግዛት አድርገውታል፡፡ እና ጎብዝ ከእንቅልፋችን ካልነቃን ኢትዮጵያ ታሪክ ልትሆን ነው ብሎ መፍራት ተገቢ አይደለምን?

እንዲህ ከሆነ ማለትም ከማሕጸኗ የተፈጠሩት የራሱዋ ልጆች ሊያጠፏት ከተነሱ ያለማመንታት የኢትዮጵያ የወቅቱ ጥያቄ ኢትዮጵያን በአገርነት ማቆየት ይሆናል ማለት ነው መልሱ፡፡

**ኢትዮጵያን በአገርነት ለማቆየት ደግሞ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?** መልሱ ኢትዮጵያውያን ተባብረን አገራችንን ከጠላት ማዳን አለብን እንደሚሆን የሁላችንም ግምት ነው፡፡ ችግር ውስጥ የምንገባው እንዴት ለሚልው ጥያቄ የምንሰጠው መልስ ከገንቢነቱ ይልቅ አጥፊነቱ ሲያይል ነው፡፡ ኢትዮጵያን ከጥፋት ሊያድን የሚችለው የትግል ዘዴ የትኛው ነው?

1. **"የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" የሚሉ ሞኛሞኝ ድርጅቶች የሚከተሉት መንገድ**

   የዚህ መላ ዋነኛ አቀንቃኙ ግንቦት 7 ነው፡፡ ግንቦት 7 ወዳጅ ለማግኘት የወያኔን ጠላት ማጥናት ነበረበት፡፡ በጥናቱ መሰረት ወያኔን የሚጠላ ሴይጣንም ቢሆንም ብንጠጋውም ይጠቅመናል ብለው የፈረጁት ሻቢያን (ኢሳያስን) ሆነ፡ ፡ ሻቢያ ግን ኢትዮጵያን ከወያኔ በላይ እንደሚጠላ ለግንቦቴዎቹ አልተከሰተላቸውም፡፡ሌላ ሊሰመርበት የሚገባው ዕውነታ ግንቦት 7 ወያኔን በሻቢያ እገዛ ሊያሸንፍ ቀርቶ ራሱ ሻቢያ ያለ የሌለ ጦሩን መዞ ወያኔን ማሸነፍ ከቶም አልተቻለውም፡፡ ዋናው ጉዳይ የኢትዮጵይን ሕዝብ ነጻ አወጣለሁ ባዩ ይህ የግንቦት 7 ለምን እንደ አይጥ ከሻቢያ ጉድጓድ ተወሸቀ? እውን ግንቦት 7 ሻቢያ የከፋ የኢትዮጵያ ጠላት ስለመሆኑ አልገባው ይሆን? ገባውም አልገባው ግንቦት 7 የተከተለው የትግል መንገድ የማሞ ቂሎን ጨዋታ ነው፡፡

2. **የወያኔን ሕገ-መንግስት ተቀብለን በሰላማዊ ትግሉ ብቻ እንጥለዋለን የሚሉ**

   በዚህ ጥላ ስር በርካታ ባገር ያሉ ድርጅቶች ቦታውን አጣበው ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ በሰላማዊ ሰልፍ ወያኔን እንጥለዋለን ባይ ናቸው፡፡ አንዳንዱ ምርጫው ላይ በመሳተፍ ወያኔን እናሸንፋለን ይሉናል ይህ ሙከራ እንዳልሰራ በተደጋጋሚ እየታየ፡፡ ሰላማዊ ሰልፍ በራሱ እንደ ዋነኛ መታገያ መንገድ ከተወሰደ የፓለቲካ ግድፈት አለው፡፡ በሰላማዊ ሰልፍ ብቻ የተገረሰሰ ስርአት አላየሁም፡፡ አላነበብኩም ወይም አልሰማሁም በወሬም ደረጃ፡፡ ምናልባት ወደፊት በምድረ ኢትዮጵያ ይሳካ ብለው የሚያምኑ ገራገሮቹ የፓለቲካ ቀመሩ ያልተገለጸላቸው ጉደና ድርጅቶች ብቻ ናቸው፡፡

3. **በዲያስፓራ ጊዜአዊ መንግስትን ወይም ጊዜያዊ ሸንጎ በመመስረት ወያኔ ሲወድቅ እንተካዋልን የሚሉ**

   የበሬ ቆለጥ ይወድቅልኛል ብላ እንደጠበቀችው አውሬ መስል ናቸውና ቢሳቅባቸው ማዘን የለባቸውም፡፡ ወያኔ ቢወድቅ ባገሩ በሜዳው ያለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊመሩት የሚችሉ ዜጎች ያጣ ይመስል ዲያስፓራን እንደ

ወሳኝ ሃይል ማሰቡ እብደት ይመስላል፡፡ እነዚህ ስብስቦች ምንኛ ስልጣን ለመያዝ እንደፈለጉ የድርጅታቸው ስም አመላካች ነው፡፡ የሚያስቁ አሳዛኝ ፍጥረቶች ናቸው፡፡ ስለነዚህ ማውራት ጊዜ ማባከን ነው፡፡

4. **የአረቡን ምሳሌ ተከትለን ወያኔ እንጥላለን የሚሉ**

በዘመናት የሚቆጠር የትግል ልምድ እንደሌለን ይመስል፡፡ አደዋ፣ የ66 አብዮት . . . ላለም ጭቁን ሕዝቦች ታላቅ ትምህርትና ተመክሮ ነው፡፡ ግብጾች፣ ሊቢያውያኖች፣ ሌሎቹም ከኛ የ66 አብዮት ቢማሩ ኑሮ ዛሬ ዲሞክራሲያዊ መንግስት በመሰረቱ ነበር፡፡ በኛ አገር የታየውን ስህተት ደገሙት፡፡

5. **ለውጥ ለማምጣት ያለ ኤሌክትሮኒክስ ሌላ መንገድ የሌለ ይመስል ትግልን በቴክስት የሚሉም አሉ**

የዚያን የግብጽና ቱኒዚያ ሕዝብ ንቅናቄ ወቅት በተለይ በዲያስፓራው "ቢቃ" የሚል የተቂት ግለሰቦች ክለብ በስልክ ቴክስት በማድረግ ወያኔን ለመገልበጥ እንችላለን ብሎ ጥቂት ቀልቦች መሳቡን እናውቃለን፡፡ በዲያስፓራ ተቀምጦ በሪሞት (ከሩቁ) የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘራፍ ሊይሰኙት አልመው ነበር፡፡

6. **በኢትዮጵያ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ትግሉ ሁለ-ገብ መሆን አለበት ይላል ኢሕ አፓ**

በዚህ የትግል ስልት የሚያምን ብቸኛ ድርጅት ኢሕአፓ ነው፡፡ ይህ ድርጅት የሰላሙ መንገድ ከሰራ ካመጽ ትግል ሰላማዊው ትግል ይሰምር ዘንድ ይጥራል፡፡ ሰላማዊው ትግል የማይሰራና ገዢውም ክፍል አሻፈረኝ ባይ ሲሆን ያመጻውን ትግል ለማፋፋም ሕዝቡን ያበረታታል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ዘዴዎች ከንቱ መሆናቸውን በማስረጃ ያቀርባል፡፡ ድርጅቱ ለሰላሙ ትግልም ሳይቀር አባላቱንና አመራሩን መስዋእት አድርጉአል፡፡ በፊልሚያውም ሂደት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ገብሯል፡፡ በዚህ ቀውጢ ትግል ውስጥ 99% የሚሆኑ አመራሮቹን ሕይወታቸውን ሰውተው አልፈዋል፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያን ነጻ የሚያወጣው ትግል ሁለ-ግብ ትግል ነው ብሎ ኢሕአፓ በሚገባ ያምናል፡፡ ሃቁም ይሄው ነው፡፡

ነገ ደግሞ ሌላ አይነት አዲስ የትግል ዘዴ ነው ብሎ ሌላ አዲስ ድርጅት አይመጣም አልልም፡፡ ትአገራችን የትግል ዘዴዎችንንና አዳዲስ ድርጅቶችን የሚያመርት ፋብሪካ ባለጸጋ ነችና እድሜ ሰጥቶን ታምራቸውን ለማየት ያብቃን፡፡ ዘዴዎችና ድርጅቶች አንደ ሙጃ ሲያበቅሉ ደግሞ የሕዝቡን ድል ማራዘሙ የማይታበል ሃቅ ነው፡፡ ሙጃ የማይረባውን ያህል የድርጅቶችና የትግል ዘዴዎች መበራከትም የሙጃ ያህል አይረቡም፡፡ አውነት እውነት እላችዋለሁ ያለ ሁለ-ገብ ትግል ኢትዮጵያችን ነፃ ትወጣለች ተብሎ ማለም የትግሉን መንገድ መሳት ወይም ማሳት ነው፡፡

**እና የኢትዮጵያ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ኢትዮጵያን በኢትዮጵያዊነቱዋ ገትሮ ማቆምና ማቆየት ነው፡፡ ይህ እንዲሳካ ደግሞ ደንቃራ ሆኖ የቆሙብንን ወያኔንና ሆዳም ደጋፊዎቹን ላንዴና ላንዴ ጠራርገን ከምድረ ኢትዮጵያ አጥፍተን ለዘላለም የምንመኘውን ሕዝባዊ መንግስት እውን ማድረግ ነው፡፡**

ወደ አርስቱ ስመለስ ስለ ኢሕአፓ ታሪክ መጻፍ ጉዳይ ልመለስ፡፡ ኢሕአፓ ለምን ታሪኩን አይጽፍም የሚል ጥያቄ ይሰማል፡፡ ይህን ጥያቄ ወይም አስተያየት የሚሰጡ ሁለት ወገኖች ያሉ ይመስላል፡፡ አንደኛው ጥያቄውንና አስተያየቱን የሚሰጡት አባላቱና ደጋፊዎቹ ሲሆኑ ሁለተኞቹ ደግሞ ጠላቶቹ ናቸው፡፡ የአባላቱና የደጋፊዎቹ ፍላጎት ታሪኩ መጻፉ ለወጣቱ ትወልድ ትምህርት ይሆናል ከማለት ነው፡፡ መነገር ያለበት ሳይነገር እንዳይታለፍ ከሚል ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡ ለቀጣዩ ትውልድ የመታገያው እንብርቱ ኢትዮጵያ ስለመሆኗ አስምሮ ለመናገር ነው፡፡ በጅርጅቱ ውስጥ በሺ የሚቆጠሩ አባላቱና አመራሮቹ በጀግንነት ለኢትዮጵያ ሕልውናና ለዲሞክራሲ መስፈን ሲሉ ውድ ህይወታቸውን ሰውተዋል፡፡ የነዚህ ጀግኖች ታሪካ መከተብ አለበት ብለውም ስለሚያስቡ ነው፡፡

**በተቃራኒው ደግሞ የኢሕአፓ ጠላቶች ለምን ታሪኩ እንዲጻፍ ወይም ለምን ታሪኩን ለመጻፍ አንደሚደከሙ ለማወቅ ጥናት መቀመጥ አይጠበቅብንም?** እነዚህ አፍራሽ ሰዎች በመጀመሪያ የኢሕአፓን ታሪክ አጥቁሮ የማቅረብ ግዴታ ከወያኔ ተለግሶላቸዋል፡፡ አላማቸው ኢሕ አፓን በመምትት ኢትዮጵያዊነትን ለማምከን ነው፡፡ በዚያ ዘመን

የተሰራውን ግፍ ሊያጋልጥ የሚችለው ኢህአፓ ስለሆን ስሙን በማጥፋት ታማኝነቱን በማሳጣት የሰራነውን ግፍ ለመካድ እንዲያስችላቸው ስለሚመስላቸው ነው፡፡የግፍ መዝገባቸው በኢሕአፓ ቤተመዘከር አለ፡፡ የደርግ ርዝራዦች አገር አጥፊ ከሆነው ወያኔ ይልቅ የኢትዮጵያ አለኝታ የሆነውን ኢሕአፓን ደመኛ ጠላታቸው አድርገው ይታገሉታል፣ “ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆን” መስሎአቸው ነጋ ጠባ ስለ ኢሕአፓ ሚርት ሲያስካኩ ይውላሉ ያድራሉ በከንቱ!

ሌላው የጊዜው የጠላት ዘዴ ኢሕአፓ ታሪኩን መጻፍ አለበት የሚል ጫጫታ ማስተጋባት ነው፡፡ ኢሕአፓ ታሪኩን በመጻፍ እንዲጠመድና ከዋነኛውን ትግሉ እንዲዘናጋ ነው፡፡ ኢሕአፓ ከመሰረታዊ ትግሉ አይዘናጋም፡፡ ታሪኩ መጻፍ ተገቢ ቢሆንም የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ የኢሕአፓን ታሪክ መጻፍ ሳይሆን ኢትይዮጵያን ከጠላቶችዋ በመመከት ሕዝባዊ መንግስትን እውን ማድረግ ነው፡፡ ወያኔና ደጋፊዎቹ የኢሕአፓን ታሪክ አጣመው በመጻፍ ላይ ናቸው፡፡ ኢሕአፓም ሆን ብለው ያንሸዋረሩትን ታሪኩን እንዲያርም ሊያታልሉት ይፈልጋሉ፡፡ ከዋናው ትግሉ ሊያዘናጉት ይጸልያሉ፡፡ ኢሕአፓ ገና ሳይወለድ የኤርትራ ነጻ አውጭዎችን እንደፈጠረ የሚተርኩ ጉደኛ ሰዎች በየፓል ቶኩ ፈልተዋል፡፡ ወያኔ ኢሕአፓ ነው የሚል አንድ ጸሃፊ በቅርቡ የውሸት ጭቃውን ባንዳንድ ድሕረ-ገጾች ላይ አንጠባጥቧል፡፡ ስለ ኢሕአፓ ከሃዲውን አንጃ ብርሃነ መስቀል ለመፈታት ሲል ለደርግ የተማጸነበትን ዝርክርክ ጽሁፍ መሰረት አድርጌ ኢሕአፓን አጋልጣለሁ ብሎአ ቀጠሮ ሰጥቶናል፡፡ እኛም ውሸቱን ሰምተን መልሰን እንደ ኮሶ ልንግተው ተስፋ እንሰጠዋለንና በርትቶ ይጻፍ፡፡ ጽሁፉ ባማርኛ ሳይሆን በእንግሊዝኛ ስለሆነ ሊያማን የፈለገው ለፈረንጆቹ ይመስለኛል፡፡

ኢሕአፓ ታሪኩን መጻፉ ተገቢና የሚጠበቅም ቢሆን ግን የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄው ከቶ ሊሆን አይችልም፡፡ ኢሕአፓ ታሪኩን ከመጻፍ የላቅ የአገር ማዳን አንገብጋቢ ስራ ላይ ነው ያለው፡፡ ኢሕአፓ ላንዳፍታ አገርን ከማዳን ፍልሚያው በሚርተኞች አዘናጊ ሴራ የማይፈታ በመከራ የተፈተነ ያገርና የሕዝብ አለኝታ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ራሱን ከሚርተኛ ዋሾች መከላከል የለበትም ማለት አይደለም፡፡

የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ኢትዮጵያን ማዳን ብቻ ነው፡፡